በዱብሊን ስምምነት ምክንያት በአመት በ10ሽዎች የሚቆጠሩ ስደተኞች በአውሮፓ አገራት ይንቀረቀባሉ። ስዊዘርላንድ የዱብሊንን ስምምነት በመፈፀም የአውሮፓ አሸናፊዋ አገር ናት።በአማካይ 54 ስደተኞች ከሌላ አገር በግዳጅ ወደ ስዊዘርላንድ ተመልሰው የስደት ጥያቄያቸው ውድቅ ይደረጋል።ባለፉት ሶስት አመታት 1500 ከግሪክና ጣልያን የመጡ ስደተኞችን በመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ተቀብላ ወረቀት ስጥታለች።




www.migrant-solidarity-network.ch




በግዳጅ መመለስ መፍትሄ አይሆንም!

ሰለማዊ ሰልፍ
8ኛ ታህሳስ
በርን ከቀትሩ 2:00
ፌደራል ቤቴ-መንግስት

በግዳጅ ምላሳዎች ጊዜ የሚከሰት ግጭት አስደንጋጭ ነው።እነዚህ እሚሰደዱ ወይም እሚፈናቀሉ ሰዎች የህይወት ዋጋ የሚያስከፍል ጉዞን መቀበል ግደታቸው ነው።በግዳጅ ምለሳዎች ሰዎችን ወደማይፈልጉትና ብዙ የህይወት ዋጋ ወደሚያስከፍል ቦታ ይመራሉ።በግዳጅ ምለሳዎች የዜጎችን የአካልና የስነ-ልቦና ጤንነትን ያላገናዘቡ ድርጊቶች ናቸው።ሰዎች በግዳጅ ምለሳዎች ምክንያት ዘወትር ህይወታቸውን ያጣሉ።ባለስልጣናት በዜጎች ላይ እሚደርሰውን እግልትና የመብት ጥሰት፣ድህነት ወይም ተወልደው ባደጉበት ማህበረሰብ መገለልንን ሳያገናዝቡ በግዳጅ መመለስን ይቀበላሉ።




በግዳጅ ለመመለስ አዳድስ ህጎች ይረቃሉ።እነህዚህ ህጎች ለስዊዘርላንድ እሚጠቅሙ አይደሉም።እንደነዚህ ህጎች ከሆነ የስደተኝነት ጥያቄው ውድቅ የሆነበት ሰው ምንም አይነት ወንጀል ሳይፈፅም ከአምስት አመት ከስድስት ወርና ከዛ በላይ ለእስር ይዳረጋል።በዚህም አያበቃም።የስደት ጥያቄያቸው ውድቅ የሆነባቸው ሰዎች ከማህበረሰቡ እንድገለሉና በውስን ቦታዎች ብቻ እንድንቀሳቀሱ ይደረጋል። እነዚህን የአንድን ግለሰብ መብት የሚጥሱ እርምጃዎችን ለመውሰድ የየትኛውም ፍርድ ቤት ውሳኔ ያስፈልጋል።የባለስልጣናት የተዛባ ምልከታ አብዛሀኛውን ጊዜ በቂ ነው።የዜጎችን ያለ ፈቃድ የመኖር ፍላጎታቸውን ለመስበር በአደጋ ጊዜ ርዳታ(Nothilfe) በመስጠት ማስጠንቀቂያ ይደርሳቸዋል።እጅግ ኋላ ቀር መጠለያውና 8 የስዊስ ፍራንክ በቀን ማግኘት ከመኖር ይልቅ ለመሞት ይቀላል።የአደጋ ጊዜ እርዳታ የአዕምሮ ማሰቃያ መንገድ ነው።ሰዎችን ጤናቸው ይታወካል።




የተወሰነው ህብረተሰብ የስደት ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገባቸው እንድመለሱ ይፈልጋል።ነገር ግን ሁሉም ግዛት በአንደ አልተቀበለውም።ለዛም ነው ባለስልጣናት በስዊዝና አውሮፓ አህጉር በስደተኞች ጉዳይ ለመስማማትና ከግሎባል ሳውዝ አገራት ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር እየጣሩ እሚገኙት።ስዊዘርላንድ ሀያልነቷን ተጥቅማ አምባገነን መንግስትም ይሁን ደሞክራሲያዊ ስደተኞችን ለመመለስ የሚደረገው አካሄድ ተመሳሳይ ነው።መንግስታት ስደተኞቻቸውን በተቀበሉ ቁጥር የገንዘብ እርዳታና የፖለቲካ እውቅና ይሰጣቸዋል።ይህ ካልሆነ ስዊዘርላንድ የንግድና የፖለቲካ ማዕቀብ እጥላለሁ እያለች ትዝታለች።

